# ዝክረ ዲበኩሉ (1)

መስፍን ማሞ ተሰማ (ከሲድኒ)

ሰንበተ ጉዳ ነበር ቀኑ። ከመኖሪያዬ አካባቢ እርቄ በአንድ የባህር ዳርቻ በመንሸራሸር ላይ ነበርኩ። ያው እንደተለመደው ብቻዬን።

ሰማያዊው ሰማይ ከአፅናፍ አፅናፍ ተንጣሏል። አልፎ አልፎ በሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ የተሳሉ እሚመስሉ ምትሃታዊና ምስጢራዊ ምስሎች በነጭ ደመና መልክ ተቀርፀው ይታያሉ።

ለምሳሌ አንደኛውን የደመና ቅርፅ በአንድ ወገን ሲያዩት ለመዝለል የተዘጋጀ የተቆጣ አንበሳ ይመስላል። አይንን ከደን አድርገው ከፍተው ሲመለከቱት ደግሞ የአንበሳው ጋሜ የቴዎድሮስን ሹርባ መስሎ፤ መልኩም ተቀይሮ  መይሳውን ሆኖ ቁጭ! በትዝብት አይን ቁልቁል እየተመለከተ። ታዲያ፤

“እዚህ ፈረንጅ ሀገር ምን ትሰራለህ?” ብለው ጠየቁኝ፤ ድንገት ሳላስበው።

“ተሰድጄ ነው” አልኳቸው፤ ድንጋጤ መላ አካላቴን እየወረረኝ።

“የምን ስደት ነው፤ ሽሽት በለኝ እንጂ። ኢትዮጵያን ሽሽት። ችግሯን ሽሽት። ሰቆቃዋን ሽሽት። ዋይታዋን ሽሽት። ጥሪዋን ሽሽት። ድህነቷን ሽሽት። እንጂ ስደት አይደለም። ስደት ማለት በእኛ ሀገር በእኛ ቋንቋ እኛ ስናውቀው፤ ከጭልጋ ቡልጋ፤ ከቢቸና ደንቢያ፤ ከፎገራ ላስታ፤ ከወሊጋ መቱ፤ ከጨርጨር ለገሃር፤ ከቃሮራ ገዋኔ፤ ከቦረና የጁ፤ ከሸሬ ደብረ ብርሃን፤ ከሲዳሞ ሊማሊሞ፤ . . . እንጂ፤ ከአዱ ገነት ፈረንጅ ሀገር አይደለም። ያልታደለች እናት። የወላድ መካን። ፈሪ ትውልድ። ታሪክ ከሃዲ ትውልድ። ታሪክ አዋራጅ ትውልድ። አፅም ወቃሽ ትውልድ። በአርበኞቹ ተሳላቂ ትውልድ። . . . እና ተሰድጄ ነው አልከኝ? ስደት ነው፤ ሽሽት?” ጠየቁኝ መይሳው በሚያስገመግም ድምፅ።

ዝም። ድርግም። ማን ለአፄ ቴዎድሮስ መልስ ይሰጣል? ቀና ብዬ መመልከት ፈራሁ። ሀፍረት አሸማቀቀኝ። ኩርማን አከልኩ። አንገቴን አዙሬ አይኔን ከቴዎድሮስ አነሳሁና ወዲያ ማዶ ወዳለው ደመና ወረወርኩ።

ራሳቸው ናቸው። አፄ ዮሐንስ። ፈረሳቸው ላይ እንደተቀመጡ፤ ግራ እጃቸውን የጎራዴያቸው አፎት ላይ አሳርፈው በትዝብት ይመለከቱኛል።

ወይ ዘንድሮ?! ዝም አሁንም። ማን አፄ ዮሐንስን በሙሉ አይኑ ይመለከታል? አይኔን ሰበርኩ። ይበልጥ አፈርኩ። ይበልጥ ኩርማን አከልኩ። ሱዳን ታወሰችኝ። መሀዲ ታወሰኝ። በአፄ ዮሐንስ ታላቅ ጦር  የራደው የተርበደበደው ከሊፋ ከእምዱራማን ቤተመንግሥት እንደ ወላድ ምጥ ይዞት ሲያማምጥ ከመተማ ተወርውረው ደረሱብኝ እያለ ሲታመስ ሲተራመስ ታየኝ። አይ ጊዜ!  ደግሞም ዛሬ፤ በዚህ ዘመን፤ በእኔ ዘመን - የደም መሬት በድርድር . . . ለአል በሽር? አኬክዳማ! . . . ምነው እምዬ ማርያም የጨው ሀውልት አድርገሽኝ በዚህ ፀሀይ ሟሙቼ ከዚህ ባህር በገባሁ?

“መተማ ላይ የወደቅሁት ለአንተ እኮ ነው። ከእኔም በፊት መቅደላ ላይ ወንድሜ ቴዎድሮስ የወደቀው ለአንተው ነው። ተከብረህ እና ታፍረህ በሀገርህ እንድትኖር። በኢትዮጵያዊነትህ እንድትኮራ። በአባቶችህ መስዋዕትነት እንድትኮራ። በታሪክህ እንዳታፍር። ታሪክ ኖሮህ፤ ዳር ድንበር ኖሮህ ማንነትህ እንዲከበር። እንጂማ የጦረኝነት ሱስ ይዞን አልነበረም። ከሰሜን ደቡብ፤ ከምስራቅ ምዕራብ፤ ከሀገር ወራሪ፤ ከአንድነት አጥፊ ጋር የተሳየፍነው። ደግሞም ከሀገር በቀል የጎጥ ፈታውራሪ ጋር ስንተናነቅ የኖርነው። ጥለን የሞትነው፤ ለአንተ ነበር። ክልል ሳይሆን ሀገር እንዲኖርህ። መንደራዊ ሳይሆን ሀገራዊ መለያ፤ ዜግነታዊ መከበሪያ እንዲኖርህ። ያስረከብንህን ነፃነት እንድትጠብቅ። በሥንደቅ ዓላማህ እንድትዋብ። የኢትዮጵያ መመኪያም እንድትሆን። ከእንግሊዙ፤ ከቱርኩ፤ ከግብፁ፤ ከመሀዲስቱ፤ ከጣሊያኑ. . . ጋር የተናነቅነው ጥለን የወደቅነው፤ በአጥንታችን ካስማ በደማችን ሊሾ  ኢትዮጵያን ያቆምነው  ለአንተ ነው።  ቴዎድሮስ በመቅደላ እኔ በመተማ። ከኛም በፊት የእኛ አያት ምንጅላቶች። ከመተማም በኋላ ቢሆን አድዋ ላይ . . .” አሉና አፄ ዮሐንስ ቀኝ እጃቸውን ወደ ሰሜን አወናጨፉ። የእጃቸውን አቅጣጫ ተከትዬ ስመለከት አፄ ምኒሊክ የጦር ለምዳቸውን እንደለበሱ፤ ፈረሳቸው ላይ ጉብ ብለው፤ አይኖቻቸው አንዳች ምትሃታዊ ድባብ ለብሰው ተመለከትኩ። ከኋላቸው አያሌ ጦረኞች ይታዩኛል። ከጎናቸው ጎልቶ የታየኝን ግን ማመን አቃተኝ። አፍጥጬ ስመለከተው ፈገግ አለልኝ። የአራዳው ግዮርጊስ ራሱ ነው፤ ጦሩን እንደያዘ።

“ተናገር እንጂ። በስደት ስም ማነው ሸሸትን ያወረሰህ? በታሪክ ስም ማን ነው የእንቧይካብ ታሪክ የካበልህ? ማን ነው ወኔህን የሰለበህ? ማን ነው በኢትዮጵያዊነትህ እንድትሸማቀቅ ያደረገህ? ኢትዮጵያዊነትህን በመንደር፣ በጎጥ፣ በዘርማንዘር መታወቂያ ያስለወጠህ ማን ነው? ማን ነው ኢትዮጵያዊነቴ ተቀጥላ እንጂ ውልደቴ መታወቂያዬ ክብሬም አይደልም እንድትል ያደረገህ? የሀገርህን ዳር ድንበር በጠበቅን፣ ለኢትዮጵያ ሉዐላዊነትና ክብር በሞትን፣ ወራሪዎቿን በባንዲራዋ ድል ባደረግን፣ በባዶ እግራችን ቆላ ወርደን፣ ደጋ ወጥተን፣ ተራራ ቧጥጠን፣ ደን ሰንጥቀን. . . የኢትዮጵያን አንድነት፣ የህዝቧን ህብረት በጠበቅን . . . ዛሬ ሹምባሽና የታሪክ ከሃዲ “ነፍጠኛ ሲለን” “ቅኝ ገዥ” ገለመሌ እያለ ስም ሲሰጠን፣ በኢትዮጵያ ላይ ሲሳለቅ፣ በአንድነቷ ሲዘባበት፣ አርበኞቿን ሲያንጓጥጥ፣ ታሪኳን ሲዘረጥጥ . . . እምቢኝ ለነፃነቴ፣ እምቢኝ ለመብቴ፣ እምቢኝ ለኢትዮጵያዊነቴ፣ እንቢኝ ለታሪካዊው ታሪኬ ብለህ ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትህ . . . በሀገርህ አድባር፣ በሀገር አውጋር በሀገርህ መኻል እንደመፋለም እንደመሞት. . . . ሸሸትን ስደት ብሎ ያስተማረህ ማን ነው? ጠየቁኝ የምኒልክ ክንድ የኢትዮጵያ ግርማ፣ የኢትዮጵያ ሞገስ፣ የጀግና አርማ ራስ ጎበና ዳጩ በዚያ ቁመታም፣ በዚያ ግርማ ሞገስን ከኩራት ጋር በተላበሰው ፈረሳቸው ላይ ሆነው ከምኒሊክ ጎን እየቆሙ።

ጉድ ፈላ ዘንድሮ! ዝም። ድርግም። ማን ለጎበና መልስ ይሰጣል? ጨነቀኝ። ምነው እንደለመድኩት አልጋዬ ውስጥ ስገላበጥ በዋልኩ ኖሮ? አሁን ለጎበና ምን ብዬ ነው መልስ የምሰጣቸው? በእኔ ዘመን በእኔ ትውልድ በሆነው ቱማታ ሁሉ ተሸማቀቅሁ። በራሴ አፈርኩ። ኩርማን ሥራዬ አሳፈረኝ። ኩርማን “ራዕዬ” ቅዠቱ ታየኝ። ተግባሬም ሆነ የነገር አታሞዬም ኩርማንነታቸው ገዝፎ ታየኝ። ኩርማን መሆኔ ታወቀኝ። . . . ጎበናን ቀና ብዬ ማየት አሸማቀቀኝ። እምዬ ምኒሊክንስ የማይበት ምን አይን አለኝ? እንግዲህስ ለምኒልክ ልሳኔን የምከፍትበት ምንስ የሞራል ብቃት አለኝ? በእኔ ትውልድ በዘመኔ በቀድሞው ትውልድ (ግርማዊነታቸውንና መንግሥታቸውን ጨምሮ) ገድል እና ሥራ ላይ እንደ ዛር አናታቸው ላይ ከመስፈር፣ በነገር ከመንዘርዘር፣ ነገር ከማባዘት፣ ነገር ከመጎንጎን፣ በነገር ከመራቀቀር፣ ነገር ከመሰንጠቅ. . . በቀር በትውልዴ ለትውልድ የሚያልፍ ምን ፈየድኩ? ምን ገነባሁ? የተገነባውን ግን ሳፈርስ. . . ሳስፈርስ. . .ጥላቻን ከቂም በቀል ጋር ስኮተኩት፣ ሳስኮተኩት፣ የጎጥ ባንዲራ ሳቀልም. . .የጎጥ ባንዲራ ስሸከም፣ የጥበት የጥላቻ፣ የቂም በቀል አራማጅና ተምሳሌ ሐውልት ሳቆም. . . ሐውልት ሳስቆም ግን ኖሬያለሁ። በሀይማኖት ቢሉ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ ቢሉ በግል የገባሁበት ሀገራዊ ኪሳራ እንደውቅያኖሱ ተንጣልሎ ታየኝ። እግዚኦ!!. . .ምነው ቅዱስ ሩፋኤል ዛሬ እግሬን በሰባበረው ኖሮ? . . . አሁን ለጎበና ምን ብዬ ነው መልስ የምሰጣቸው? ተሰድጄ ነው ሸሽቼ? ለኢትዮጵያ ስል ነው ለራሴ? እያልኩ ሳሰላስል፣ ከባህሩ አንደኛ ወገን የጡሩንባ ድምፅ ሰማሁ።

ሰውነቴን ሰቀጠጠኝ። የጦርነት መለከት የተነፋልኝ መሰለኝ። የጥሪ ድምፅ የቀረበልኝ መሰለኝ። ዞር ብዬ ተመለከትኩ። የባህሩን ወደብ በመልቀቅ ላይ የነበረች እጅግ ግዙፍ መርከብ ነበረች ጡሩንባዋን ያስተጋባችው። የእኔን ቁመት የሚያካክል ፅሁፍ ጎኗ ላይ ይነበበኛል። “ጣይቱ ቡጡል የባህር ሃይል ብርጌድ - ኢትዮጵያ ” ይላል። የመርከቧ ስም መሆኑ ነው። “ጉድ ፈላ ዛሬ!” አልኩ ለራሴ። አይኔን ማመን እያቃተኝ። እየተርበተበትኩ ቀና ብዬ ተመለከትኩ። አፄ ቴዎድሮስ በቦታው የሉም። ደመናውም የለም። አፄ ዮሐንስን ወደ አየሁበት ብዞር እሳቸውም እዛ የሉም። ደመናውም የለም። አፄ ምኒሊክን ወደ አየሁበት ወደ ሰሜን ባቀና እሳቸውም እዛ የሉም፣ ራስ ጎበናም የሉም። እዚያ ላይ አይቼው የነበረው ሁሉ ተቀያይሮ፣ ደመናው ደግሞ በእጥፍ ገዝፎ ተመለከትኩ። ዶፍ ሊወርድ ይሆን እንዴ? ምፅዐት ሊመጣ? . . . ..”ሲነጋ ሲል ይጨልማል” አይደል እሚሉት እኒያ ጥንታውያኑ . . . ጠቢባኑ።

ድንገት ደግሞ ሶስቱም ፈረሶቻቸው ላይ እንደተቀመጡ፣ እጅ ለእጅ ተያይዘው፣ የጀግንነት ግርማ ሞገስን ተላብሰው፣ ከወዲያ ማዶ ሆነው ተመለከታኳቸው። አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ዮሐንስ፣ አፄ ምኒሊክ፣ እነ ጎበና ደጆን ቆመው። ። ከበላያቸው ቀስተ ደመና ይታየኛል። ቀለሞቹ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ናቸው። ቀስተ ደመና ነው ወይስ የኢትዮጵያ ባንዲራ? ደግሞ ይውለበለባል እንዴ? ከሶስቱ ጀርባ ደግሞ በቅድመ ታሪክ የማውቃቸው ነገስታት፣ እነ ላሊበላ፣ እነ ፋሲለደስ እና ሌሎችም ከነአጀባቸው በደጅንነት ቆመቀው ታዩኝ። አራዳው ግዮርጊስ ግን ፈረሱ ላይ አልነበረም። ክንፎቹን ዘርግቶ ከበላያቸው ያንዣብባል። በተዘረጋው ቀኝ እጁ በያዘው ጦር ላይም የሚውለበለብ ቀስተ ደመናዊ ባንዲራ ይታየኛል። እሱም የያዘው የኢትዮጵያን ባንዲራ ነው እንዴ? የሚያመለክተውም ወደ ምስራቅ? ጉድ'ኮ ነው! አንዳች ምስጢራዊ መልእክት አይኖቹ ውስጥ ያነበብኩ መሰለኝ። ምን ይሆን ሊነግረኝ የፈለገው? ወዴት ይሆን ይህ ሁሉ መሰናዶ?

ለሁለተኛ ጊዜ የመርከቧ ጡሩንባ አስተጋባ። ሰላማዊውን ውቅያኖስ እያተራመሰች አፍንጫዋን ወደ ምስራቅ አቀናች። በዛ ግዙፍ ሰውነቷ ባህሩን እየሰነጠቀች አንዳች ግርማ ሞገስን እና በራስ መተማመንን ስሜት ለተመልካቾቿ ሁሉ እየረጨች ተፈተለከች።

ቀና አልኩኝ። ያ ክምር ደመና ደረቱን ገልብጦ እየተጀነነ፣ እየተንጎማለለ ጉዞ ጀምሯል። የት ሄዱ? ምነው አይታዩኝም? አንዳቸውም የሉም። አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ዮሐንስ፣ አፄ ምኒሊክ፣ ራስ ጎበና፣ እነ ላሊበላ፣

የአራዳው ግዮርጊስ. . . ሁሉም የሉም። ተያይዘው የት ገቡ? ደመናው እየተጓዘ ነው። መርከቧን እየተከተለ። ደመናው የጀግኖቹ የጦር መንኮራኩር መስሎ ታየኝ። ይሆን እንዴ? . . .

አይኔን ወደ መርከቧ አቀናሁ። እየራቀች፤ እየራቀች እያነሰች፤ የምስራቅን አቅጣጫ ይዛ ስትጓዝ ታየችኝ። ደመናውስ? ደመናውም ከበላይዋ በኩራት ይቀዝፋል። ሄዱ፤ ነጎዱ፤ አድማስ ጥግ ደረሱ። ይሄኔ አንበሳው የኢትዮጵያ ኩራት፤ የኢትዮጵያ ጀግና ጎበና ዳጬ ወደ እኔ ዞረው የተመለከቱ መሰለኝ። ነጭ ጥርሳቸውን ብልጭ አድርገው ከትዝብት ፈገግታ ጋር ለቅፅበት አተኩረው ያዩኝ መሰለኝ። ስለምን ይሆን እንዲያ የተመለከቱኝ? አዝነውብኝ? አፍረውብኝ? ወይስ አዝነውልኝ? . . . ደንዝዤ ቀረሁ። መርከቧም ደመናውም ከአድማስ ወዲያ ተሻገሩ። ከአይኔ ጠፉ . . . እኔም እራሴን ይዤ በራሴ ሀሳብ ጠፋሁ።

መቼ እንደሆን ባላውቅም ወደ ራሴ ስመለስ ባህር ዳር መቀመጤን ጊዜውም ደንገዝገዝ ማለት መጀመሩን አስተዋልኩ። ጉድ ነው! የሆነውን ሁሉ አስታወስኩ። ምን ነበር ያየሁት? . . . ወይስ አላየሁም? ድንቅ'ኮ ነው ባካችሁ! አሁን ያየሁትን ለሰው ባወራ ማን ያምነኛል? ይህንን ለአራዳ ልጆች ብነግራቸውስ ምን ይላሉ?። መቼስ ፈረንጅ አምላኩ ይህንን ሲሰማ አንደኛህን ለይቶልሃል ነው የሚለኝ። ካልሆነም አንድ ሐሙስ ቀርቶሃል። ግን እርግጠኛ ነኝ አስተማሪ አለሙ ያምነኛል። እትዬ አቻሜም ያምኑኛል። ዋቅጅራም ያምነኛል። ኒቂሴም ታምነኛለች። ሽምሱም ያምነኛል።

ከተቀመጥኩበት ተነስቼ በዝግታ ወደ ባቡር ጣቢያ የሚወስደውን መንገድ ያዝኩ። ህሊናዬ በጥያቄ ተወጥሯል። ስደት ነው ሽሽት? . . . ስደት ነው ሽሽት? የትኛው ነው የእኔ?. . .

----------------------------------------------------- ተ ፈ ፀ መ -----------------------------------------------------

በያለንበት ቸር ይግጠመን!

{ይህ ፅሁፍ አስቀድሞ በየካቲት 1994 ዓ/ም (ፌብሩዋሪ 2002) በሲድኒዋ "ድንቅነሽ" መፅሔት ላይ ተነበበ። በዚህ አቅርቦት ጥቂት ቃላት ተነቅሰዋል/ተጨምረዋል እንጂ}

መጋቢት 2008 ዓ/ም (ማርች 2016)

ሲድኒ አውስትራሊያ

አስተያየት ቢኖርዎ፤ mmtessema@gmail.com